**ለ SPIKEVAX** (የሚነበበው SPĪK-văx ተብሎ ነው)
(COVID-19 ክትባት፣ mRNA) **(2023-2024 Formula)**
ተቀባዮችና ተንከባካቢዎች
የቀረበ መረጃ

SPIKEVAX ከመከተብዎ በፊት እባክዎ ይህንን የመረጃ ወረቀት ያንብቡ። ይህ ሰነድ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር የመነጋገርን ቦታ እንዲተካ ተብሎ የታሰበ አይደለም። ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።

## SPIKEVAX ምንድን ነው?

SPIKEVAX እርስዎን ከCOVID-19 የሚከላከል ክትባት ነው። SPIKEVAX አገልግሎት ላይ የሚውለው እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ነው። የ SPIKEVAX ክትባት ሁሉንም የተከተቡ ሰው ላይከላከል ይችላል።

SPIKEVAX COVID-19ን የሚያመጣውን SARS-CoV-2ን አይዘም። SPIKEVAX COVID-19 ሊያሲዝዎት አይችልም።

## SPIKEVAX መከተብ/መውሰድ የሌለበት ማን ነው?

በሚከተሉት ሁኔታዎች SPIKEVAX መውሰድ የለብዎትም፥

- ቀደም ሲል የወሰዱትን SPIKEVAXን ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት (ዋናው ሞኖቫለንት)፣ ወይም ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ከባድ የአለርጂ አፀፋዊ ምላሽ ካጋጠምዎት፣[1]
- በዚህ ክትባት በየትኛውም ግብአት ምክንያት ከባድ አለርጂ አጋጥሞ ከነበረ(**የSPIKEVAX ግብዓቶች ምንድን ናቸው?** የሚለውን ይመልከቱ)

## ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዬ ምን መናገር አለብኝ?

ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የሚከተሉትን ጨምሮ ስለ ሁሉም የጤና ሁኔታዎችዎ ይንገሩት:

- የትኛውም አላርጂዎች ካሉብዎ
- ቀደም ሲል ማንኛውንም የCOVID-19 ክትባትን ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ከባድ አለርጂ ካጋጠመዎ
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) ያለብዎ ስለመሆኑ
- ትኩሳት ካለብዎ
- የደም መፍሰስ ችግር ወይም የደም መቅጠን ካለብዎ
- የበሽታ መከላከል አቅምዎ የተዳከመ ከሆነ ወይም የበሽታ መከላከል ስርአትዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መድሀኒት እየወሰዱ ከሆኑ
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የማርገዝ እቅድ ካሉዎ
- የሚያጠቡ ከሆነ
- ሌላ ማንኛውንም የCOVID-19 ክትባት ከወሰዱ
- ከክትባት ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው የነበር ከሆነ

## SPIKEVAX የሚሰጠው እንዴት ነው?

SPIKEVAX በመርፌ መልኩ በጡንቻ ላይ ይሰጣል።

## የSPIKEVAX ስጋቶች ምንድን ናቸው?

ከባድ የአለርጂ አጸፋዊ ምላሽ የሚከተሉትን በተከተቡ የተወሰኑ ሰዎች ላይ ተከስተዋል፥ SPIKEVAX፣

[1] SPIKEVAX የተዘጋጀው ከሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት (ዋናው ሞኖቫለንት/monovalent) እና ከሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ጋር በተመሳሳይ ዘዴ ነው፣ ነገር ግን የ SARS-CoV-2 የኦሚክሮን (Omicron) ዝርያ XBB.1.5 (ኦሚክሮን XBB.1.5) ስፓይክ ፕሮቲን ያመነጫል።

የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት (ዋናው ሞኖቫለንት/monovalent) እና የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent። SPIKEVAX ከባድ የአለርጂ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስከትል የሚችልበት በጣም አነስተኛ ዕድል አለ። ከባድ አለርጂ በዋናነት የሚያጋጥመው የ SPIKEVAX ዶዝ ከተወሰደ በኋላ ካሉት ጥቂት ደቂቃዎች ጀምሮ እስከ 1 ሰአት ያክል ነው። በዚህም ምክንያት፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የክትባቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ክትባቱን በወሰዱበት ቦታ እንዲቆዩ ሊጠይቅዎ ይችላል። የከባድ አለርጂ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡

- ለመተንፈስ መቸገር
- የፊት ወይም ጉሮሮ እብጠት
- የልብ ምት መፍጠን
- በመላ ሰውነትዎ ላይ የሚፈጠር ሽፍታ
- መደበትና ድካም

ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) በጥቂት SPIKEVAXን የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን (ዋናው ሞኖቫለንት/ monovalent) እና የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ጨምሮ የ mRNA COVID-19 ክትባቶች በወሰዱ ሰዎች ላይ ተከስቷል። የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ተከትሎ ማዮካርዲቲስ እና ፔሪካርዲቲስ በብዛት የተከሰቱት እድሜያቸው ከ18 እስከ 24 ዓመት በሆኑ ወንዶች ላይ ነው። በእነዚህ አብዛኞቹ ግለሰቦች ላይ ምልክቶቹ መታየት የጀመሩት ክትባቱን በወሰዱ በጥቂት ናት ውስጥ ነው። ይህ የሚያጋጥምበት እድል በጣም ዝቅተኛ ነው። እርስዎ ወይም ልጅዎ ክትባቱን ከወሰዳችሁ በኋላ፣ በተለይም የክትባቱን ዶዝ ከወሰዳችሁ በኋላ ባሉት 2 ሳምንታት ውስጥ የትኛውም የሚከተሉት ምልክቶች ከታዩባችሁ ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ያድርጉ፡

- የደረት ህመም
- ትንፋሽ ማጠር
- የፈጣን አተነፋፈስ፣ የልብ መርገብገብ ወይም መውጋት ስሜት

በክሊኒካል ሙከራዎች SPIKEVAX፣ በሞደርና (Moderna) የ COVID-19 ክትባት (ዋናው ሞኖቫለንት/ monovalent)፣ እና በሞደርና (Moderna) የ COVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ላይ ሪፖርት የተደረጉ የጎኒዮሽ ውጤቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፥

- ክትባቱ የሚሰጥበት የሰውነት ክፍል አካባቢ የሚፈጠሩ አሉታዊ ምላሾች፡ ህመም፣ ክትባቱ የሚሰጥበት እጅ የብሽሽት ክፍል መቆጣትና እብጠት፣ እብጠት (የሰውነት መደደር) እና መቅላት
- ጠቅላላ አሉታዊ ምላሾች፡ ድካም፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ ህመም፣ የመገጣጠሚያ ህመም፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ማቅለሽለሽና ማስመለስ፣ ትኩሳት፣ እና ሽፍታ

ሪፖርት የተደረጉ ሌሎች የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፥

- ከባድ አለርጂ
- ዩሪቲካሪያ (የሚያሳክ ሽፍታ)
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- ከክትባቱ ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው ያውቁ ከሆነ

SPIKEVAX ክትባት የሚያስከትላቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች እነዚህ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። እርስዎን የተመለከቱ የጎንዮሽ ጉዳቶችን አስመልክቶ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ። የጎኒዮሽ ጉዳቶችን ለክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት (VAERS) በስልክ ቁጥር 1-800-822-7967 ወይም https://vaers.hhs.gov ሪፖርት ያድርጉ።

**<u>ነፍሰ ጡር ወይም የማጠባ ቢሆንስ ምን ይሆናል?</u>**
ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የሚያጠቡ ከሆነ ስለ አማራጮችዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

የእርጉዝ ተጋላጭ ምዝገባ ክፍል አለ። ልክ እርግዝናዎን እንዳወቁ

በስልክ ቁጥር 1-866-MODERNA (1-866-663-3762) በመደወል ምዝገባ ክፍሉን ያነጋግሩ ወይም እርስዎን ወክሎ ምዝገባ ክፍሉን እንዲያነጋግርልዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።

**<u>የSPIKEVAX ግብአቶች ምንድን ናቸው?</u>**

SPIKEVAX የመሚከተሉትን ግብአቶች ይይዛል፡

- ሜሴንጀር ሪቦኒውሴሊክ አሲድ (mRNA)፣
- ሊፒዶች (SM-102፣ ፖሊቲሊን ግሊኮል [PEG] 2000 ዲሚሪስቶይል ግሊሴሮል [DMG]፣ ኮሌስትሮል እና 1,2-distearoyl-sn-glycero-3-ፎስፎኮሊን [DSPC])፣
- ትሮሜታሚን
- ትሮሜታሚን ሀይድሮክሎራይድ
- አሴቲክ አሲድ
- ሶዲየም አሴቴት ትራይሀይድሬት
- እና ስኳር

እና ስኳር

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ፣ www.spikevax.com የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ፣ ወይም በስልክ ቁጥር 1-866-MODERNA (1-866-663-3762) ይደውሉ።

የተመረተው ለ፥
Moderna US, Inc. Princeton,
NJ 08540

©2023 ModernaTX, Inc. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።
SPIKEVAX የ ModernaTX, Inc. የንግድ ምልክት ነው።
የፈጠራ ባለቤትነት(ቶች): www.modernatx.com/patents
የተሻሻለበት ቀን: መስከረም 2023